**Amharic**
መጋቢት 2023

# በምሽት ማታ፣ በሳምንቱ መጨረሻ ወይም በህዝባዊ በዓላት

# ጊዜ የህክምና እርዳታን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል





የአውስትራሊያ የህክምና አሰራር ሥርዓት ውስብስብ ነው። እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ ከታመሙ፣ የትኛውን የጤና አገልግሎት መጠቀም እንዳለብዎት፣ ክፍት የሚሆኑበትን የስራ ሰዓት እና ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስወጣ ማወቅ አለብዎት። ይህ ሰነድ በአውስትራሊያ ውስጥ ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ የህክምና እርዳታ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የበለጠ ለማወቅ ይረዳዎታል።

**ማሳሰቢያ በቪክቶሪያ ውስጥ ላሉ ጥገኝነት ጠያቂዎች ፡-**
በሆስፒታል የድንገተኛ ህክምና ክፍል ውስጥ ነጻ ህክምና ማግኘት ትችላላችሁ። የሌሎች የህክምና አገልግሎቶችን ማግኘት እና አለማግኘትዎ በያዙት የቪዛ አይነት መሰረት ይወሰናል። እርስዎ የሚያገኙት አገልግሎቶች በጊዜ ሂደት ሊለወጡ ይችላሉ፣ ስለዚህ እባክዎን ምን ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅ የጉዳይ ሰራተኛዎን በማነጋገር ያረጋግጡ።

## ከታመሙ ምን ማድረግ እንዳለብዎት የዶክተርዎ ህክምና ማእከል ግን ተዘግቷል።

**በምሽት ማታ፣ በሳምንቱ መጨረሻ ወይም በህዝባዊ በዓላት ላይ፣**

**ከታመሙ እና ሀኪም ከፈለጉ፣ ከእነዚህ ነጻ የህክምና አገልግሎቶች**

**አንዱን መጠቀም ይችላሉ።**

**በስልክ እርዳታ ለማግኘት፡-**

- ተረኛ-ነርስ (Nurse on call) ላይ 1300 60 60 24 (በቪክቶሪያ ውስጥ)
- ከስራ ሰዓት በኋላ የዶክተር (GP) የእርዳታ መስመር (healthdirect) በስልክ 1800 022 222

**ሀኪም ወደ ቤትዎ እንዲመጣ ከፈለጉ፡-**

- የቤት ውስጥ ዶክተር (The Home Doctor) በስልክ 13 74 25 (በቪክቶሪያ ውስጥ)

**እንግሊዘኛ የማይናገሩ ከሆነ፣ የነጻ አስተርጓሚ እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያገኙ ሊረዳዎ ይችላል።**

STEP 1 ወደ TIS ሃገራዊ/ናሽናል በስልክ 131 450 ይደውሉ እና አስተርጓሚ እንዲቀርብልዎት ይጠይቁ።

STEP 2 የ TIS አስተርጓሚ ማነጋገር ወደ ሚፈልጉት አገልግሎት እንዲደውል ይጠይቁ።

በመጋቢት 2023 ዓ.ም የተዘጋጀ

# ሆስፒታል
# የድንገተኛ ክፍል

የድንገተኛ ክፍል ወዲያውኑ በአስቸኳይ መታየት ላለባቸው የህክምና ችግሮች ነው። ለምሳሌ፦

- የመተንፈስ ችግር እያጋጠመዎት ነው፣።
- የማይቆም የደም መፍሰስ እያጋጠምዎት ነው።
- አጥንትዎ ተሰብሯል ወይም ጭንቅላትዎ ተጎድቷል።
- የደረት ህመም ወይም ውጋት እየተሰማዎ ነው።

**የህክምና ድንገተኛ አደጋ ካለብዎ አምቡላንስ እንዲመጣልዎ ለ 000 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያው ወደሚገኝ ሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ያምሩ።**

የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ክፍሎች ሁሌም ክፍት ናቸው - **በእያንዳንዱ ቀን - በሁሉም ቀን እና ሌሊት** ነገር ግን ህመምተኞች በደረሱበት ቅደም ተከተል ሳይሆን በከፍተኛ ደረጃ የታመሙትን ቅድሚያ ሰጥተው ስለሚያክሙ ድንገተኛ ክፍል ውስጥ ለረጅም ጊዜ መጠበቅ ሊኖርብዎ ይችላል።

**ወደ ድንገተኛ ክፍል ሲሄዱ፦**

- ካለዎት፣ Medicare (የሜዲኬር) እና የጤና እንክብካቤ ካርድዎን ይዘው ይሂዱ።
- የሚያስፈልግዎት ከሆነ አስተርጓሚ ይጠይቁ።
- ማንኛውንም ነገር ከመብላትዎ ወይም ከመጠጣትዎ በፊት ሰራተኞቹን ይጠይቁ።

**000 ቁጥር አድርጎ ከማንኛውም ስልክ ለመደወል ሁል ጊዜ ነጻ ነው።**




# አምቡላንስ

## ማንኛውም ድንገተኛ የጤና እክል ሲያግጥምዎ በ 000 ወደ አምቡላንስ ይደውሉ።

ድንገተኛ የጤና እክል እርስዎ ወይም ሌላ ሰው ከባድ ሕመም ወይም ጉዳት ሲደርስባቸው እና በፍጥነት እርዳታ ሲፈልጉ ነው።

**በሚከተሉት ምክንያቶች ወደ አምቡላንስ አይደውሉ፦**

- በጣም በፍጥነት እርዳታ የማያስፈልግዎት ከሆነ።
- ድንገተኛ ላልሆነ የጤና አገልግሎት ቀጠሮ መጓጓዣ የሚያስፈልግዎት ከሆነ።
- ወደ ድንገተኛ አደጋ ክፍል እራስዎ መድረስ የሚችሉ ከሆነ።

**የአምቡላንስ አገልግሎት በጣም ውድ ሊሆን ይችላል።**

በአንዳንድ አስተዳደር ግዛቶች አምቡላንስ በነፃ የሚሆነው፦

- Centrelink (የሴንተርሊንክ) የጤና እንክብካቤ ካርድ ካለዎት።
- የጡረተኛ የቅናሽ ካርድ ካለዎት።
- የክልልዎ የአምቡላንስ አገልግሎት አባል ከሆኑ።
- ወጪውን የሚሸፍን የግል ኢንሹራንስ ካልዎት።

**Medicare ለአምቡላንስ አይከፍልም።**




በ ACT መንግስት ለተዘጋጀው እና ይህንን ጽሁፍ በማዘጋጀቱ ሂደት ለተጠቀምንበት 'Using health services in the ACT' ሰነድ እውቅና መስጠት እንፈልጋለን።

centre for culture, ethnicity &health